# ይድረስ ለዶክተር ነጋሶ ጊዳዳ

የአዲስ አበባ 10ኛው ቅንብር እድገት መሪ ዕቅድ አሳዛኝ ውጤት / A tragic consequences of the 10th Addis Ababa Intigrated development master plan / ማስጠንቀቂያ ለወደፊቱ በሚል ርእስ የጻፍከውን በአጽንኦት ተመልክቸዋለሁ።
ባቀረብከው ጽሑፍ መግቢያው ላይ ታሪካዊ ተብዬ ትረካ አቅርበሃል። የታሪክና የጎሳ ጥናት "ምሁር" መሆንክን ስምቼ ከፍተኛ ትዝብት አሳድርሮብኛል።

ሰለ አዲስ አበባ ከተማ አመሰራረት ጽፈሃል። ስለምን እንጦጦ እንደተመረጠ ግን ምንም ሳትል አልፈኻል። ንጉሥ ምኒልክ ከእነዋሪ ወደ እንጦጦ የመጡበት ዐቢይ ምክንያት እንጦጦና ከአዲስ አበባ በስተምዕራብ ያለት የመናገሻና የወጨጭያ ተራርች የኢትዩጵያ ታላላቅ ነገሥታት የነ አጤ ዳዊት (1382-1411) ተከታዩቹ ዋና መቀመጭያ፤ የአጤ ዘርአ ያዕቆብ (1434-1468) የትውልድ ስፍራ በመሆኑ ነው። በተለይ የመናገሻ ደን አስቀድሞ በአጤ ዘርአ ያዕቆብ የተተከለ መካነ ዕፀዋት (Botanical garden) መሆኑንና ቀጥሎም በአጤ በእደ ማርያም (1468-1478) የተስፋፋ መሆኑን ዜና መዋዕሉ በሰፊው መዝግቦ አቆይቶናል። በዚሁ አካባቢ የጥንት አቢያተ ክርስቲያን ፍርስራሾች በብዛት ይግኛሉ። የየካ ፍልፍል ዋሻ፣ የመናገሻ ገዳም፣ ያዳዴ ወዘተረፈ መጥቀስ ይቻላል።

በንጉሥ ሣህለ ሥላሴ (1813-1847) በእንጦጦና አካባቢዋ የተደረገውን የማስገበር ዘመቻ በተመለከተና የእንግሊዝ ንግሥት ቪኮቶሪያ 34 መልክተኞች መሪ የነበረው ሻምበል ሃሪስ እንደዘገበው እያልክ በመግቢያነት ጽፈሃል።
ዳሩ ግን የኦነግ ነፃ አውጭ ግንባር ተብዬውና የነጭ ፀረ ጥቁር ሞግዚቶቹ እንደ ቦኒ ሆልኮምብ (Bonnie Holcomb) እና ሲሳይ ኢብሳ የተባሉት ቅጥረኞች ዓይናቸውን በጨው አጥበው፣ የውሸት ታሪክ ፈጥረው ለ"ኦሮሚያ ሪፑብሊክ" ምስረታ ይረዳል ብለው ያነበነቡትን ጸረ-ኢትዩጵያ በሬው ሳም ወለድ የጥላቻ ዘመቻ ጥንቅር ማለትም Bonnie K. HOlcomb and Sisaye Ibssa: *The invention of Ethiopia*, 1990, Red Sea Press በታሪካዊ ሰንድነት በሽፍንፍን መጥቀስህ ትልቅ ቅሌት ሲሆን ያንተንም አቋም  በግልጽ ያስረዳል።

በመቀጠልም የንጉሥ ሣሕለ ሥላሴ ሠራዊት በኦሮሞ አካባቢ ባደረገው "የመስፋፋት ጦርነት" በተለይም በእንጦጦ ተራራ ከአውሮፓውያን የተሰጠውን ጠመንዣ አጠቃቀም ሲለማመዱ የእንግሊዝ መልክተኞች በሩቅ መነጽር ተመልክተው የዘገቡት ነው በማለት ፍጹም የፈጠራ ወሬ ስምተህ አናፍሰሃል። ይህም ያልተጻፈን ማንበብ ነው። ሻምበል ሐሪስ The Highlands of Ethiopia 1844 በሚል ርእስ በሸዋ የእንግሊዝ መንግሥት ኢምባሲ መሪ ሆኖ 18 ወራት ቆይቶ ሲመለስ የጻፈውን ያንበቡት ወገኖች በወቅቱ ከፍተኛ ነቀፋ ስንዝረውበታል። ተልእኮው የከሸፈ ነው፣ የብሪታኒያ መልክተኞች የንጉሡን ዘመቻ በመርዳት ጋሎች እስረኞች እንዲሆኑ ረድተሃል፣ በስጦታ የቀረቡት ጠመንጃዎች ጥቅም ላይ ውለዋል ወዘተረፈ ተብሎ ትችት ቀርቦበት ምላሽ ሰጥቷል። በሁለተኛው እትሙ መግቢያ ላይ የተሰነዘሩብኝ ነቀፋዎች ሁሉ በልዩ ወሬዎች "Strange-Stories" ላይ የተመሠረቱ ናቸው በማለት አጣጥሎ አቅርቦታል፤

**...**that the Britsh officer in Shoa, assisted the king in making prisoners among the Gallas, that the fiel-pice, which which has been presented to the king, and was therefore no longer under the controol of the embassy, was employed to battle down villages, and, to effect the triumpf of Sahele Selasse over his refractory subjects and heathen neighbours.

The slaughter was not perpetrated by means of gallop-guns, which went not on the expidation at all, but was left left by the king at his ppalace newly errected.

ሐቁ ግን የሸዋ ገዥዎች ከንጉሥ ሣህለ ስላሴ በፊት ጀምሮ ጠመንጃ ሲያገኙ የነበሩት ከጎንድር፣ ከትግሬና ከታጁራ ጀበርቲ ነጋዴዎች ስለነበር የእንግሊዞች ትንሽ ስጦታ ይህን ያህል ወሳኝ ሚና አልነበረውም። በሰሜን ምሥራቅ አፍሪቃ የነበሩት መስፍንቶች፤ በደቡብ ምዕራብ ማለትም በጅማ፣ በወለጋ ወዘተ. ያሉትን የወረሞ መሳፍንቶች ጨምሮ ጠመንጃና ልዩ ልዩ ሸቀጦችንና የእስልምና ሃይማኖትን ያገኙት ከቦንጋ ከጎንደር-መተማ ስ፡ራራ ነጋዴዎች መሆኑ ይታወቃልና።

ስለ ጠመንጃ ከተነሳ ዘንድ በሸዋ መርድ አዝማች አብዬ ከጎንደር በራስ ወልደ ልዑልና አየለ ወሰኑ መሪነት ለማስገበር የተላከበትን ዘማች ሠራዊት አሸንፎ ከስድስት መቶ ጠመንዣ በላይ መማረኩ ይታወቃል። የሸዋ ሠራዊት ጠመንዣ ያዥ በዚያ ዘመን የነበረውን ጠንቅቆ የሚያውቅ አላሚ ተኳሽና ባሩድም ራሱ የመስራት ችሎታ ማዳበር እንደጀመረ ተረጋግጧል።

# የሸዋ አካባቢ መንግሥት ለምን ተፈጠረ?

የኢትዮጵያ አጤ ማዕከላዊ መንግሥት በ16ኛው ምዕተ ዓመት ከደረሰበት የጅሃድ ወረራ ምንም ሳያገግም በተከተለው የጋላ ወራሪ ሰፋሪ ምክንያት ፍጹሞ ስለተዳከመ ከሸዋ የረርና እንደግብጣን (መናገሻ ተራራ) ዋና መቀመጭያው ወደ ጎዣምና ጎንደር ስለተዛወረ ቀጥሎም በየጁ ወረሞ፣ በትግሬና በቋራ መሳፍንቶች መካከል በተደረገው የሥልጣን ሹክቻ ያጤው ሥልጣን ከስሞ ዘመነ መሳፍንት ተከሰተ።

የሸዋ አውራጃ ባላባቶች ለየራሳቸው የነበሩትን ባንድነት ለመግዛት በነጋሢ 1665 ዓ.ም ተጀምሮ ደረጃ በደረጃ እሰከ ሰባተኛው ገዥ ንጉሥ ሣህለ ሥላሴ (1813 እስከ 1847 ዓ.ም) ድረስ ሸዋን አንድ ለማድረግ ከፍተኛ ዘመቻ ተደረገ። ነጋሢ በመንዝ ውስጥ ብቻ የነበሩትን ባላባቶች ለማስገበር ከ10 ዓመታት በላይ ወስዶበታል። የተሳካለትም የጎንደሩን አጤ ኢያሱ አድያም ሰገድ (1682-1706) ርዳታና ዕውቅና በማግኘቱ ነበር። መርድ አዝማች አምኃየስ የጠራን፣ የቡልጋን፣ የምንጃርን፣ የበረኽትን፣ የተጉለትን፣ የወግዳን ባላባቶች በማስገበር የሸዋን ግዛት መልሶ አንድ ሲያደርግ ልጁ መርድ አዝማች አስፋ ወሰንም የሞረትን፣ የመራቤቴ ኮራንና የግራርያን ባላባቶች እስከ አባይ ድረስ አስገብረ። ልጁ ራስ ወሰን ሰገድ ከሸዋ አልፎ ጎንደርን ለመያዝ ሲዘጋጅ በአጭሩ ተቀጭቷል። በጥቅሉ ሸዋ ራሱን ችሎ አንጻራዊ ስላም ኖሮት፣ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ እድገት በማስመዝገቡ ነው ፈረንሳይና እንግሊዝ ግንኙነት ለመፍጠር የፈለጉትና መልክተኛ የላኩት።

በሸዋ መንግሥት የተደረገው የመስፋፋት ዘመቻ ሳይሆን በግራኝ አሕመድና በተከተለው የጋላ ወረራዎች መስፈር ተበታትኖ በየአውራጃው ባላባቶች ለየብቻ ተከፋፍለውት የነበረውን ጥንታዊ ግዛት መልሶ የማስገበርና የማቅናት (Reconquesta) መሆኑ በግልጽ መታወቅ አለበት። የወረሞ ጠባባ ጎሠኞችና ነፃ አውጪ ተብዬ ቅጥረኞች የሚያናፍሱት የኦሮሚያ ግዛት በአማሮች ቅኝ መገዛት በሬው ላም ወለድ ነው። በቱላማ ወራሪ ሰፋሪዎች ከ1567 ዓ.ም ጀምሮ የተያዘባቸውን ለም መሬት ለማስመለስ የተደረገ ተገቢ ዘመቻ ነው።

# ፊንፊኔ አዲስ አበባ አይደለም

ዶክተር ነጋሦ ሰለ ፊንፊኔና አዲስ አበባን በሚበለከት ሻምብል ሐሪስ ዘገባ ጠቅሰሃል። ይሁንና ዘገባውን ቀንጨብ አድርግህ ከመተረክ ይልቅ በጥልቅ በትመረምረው ኖሮ በፊንፊኔ ሸለቆና በኤካ ሸለቆ መካከል 55 ማይል ወይም 77 ተኩል ኪሎ ሜትር ለ14 ሰዓታት ተጓዝን ይላል። ( During fourteen hours passed in the saddle, above fififty miles of country had been passed over, and the weary forces finally halted in the Ekka valley'Volume two- Chapter Twenty three) የእንጦጦ ተራራ መሸሻ ምሽግነትን ገልጾ አዳር የካ ኮረበታ ላይ ተደርጎ በማግስቱ ደግሞ በሩቅ ማይል ርቀት ላይ ወዳለው ሱሉልታ ሞሎ ፊልዳ አጠገብ የሸሹት ተደመሰሱ እያለ የተረከው የተዘበረቀ ነው። በአንድ በኩል የፊንፊኔ ጥቅጥቅ ያለ ደንና የወንዞች ፏፏቴ፤ በሌላ በኩል በሜዳው ላይ ስለነበረው ድርስ ሰብልና መኖሪያ ቤቶች መጋየት፣ በፊንፊንኔና ኤካ መከከል ያለው ርቀት 77 ኪሎ ሜትር ተጉዘው ጥልቅ የወንዝ ዳሮችን በከፍተኛ ችግር ተሻግረው ወዘተረፈ እያለ የተረከው ይልቁንም ጎጀብ ወንዝ ጁባ መሆኑን አረጋገጥኩ እንዳለው ፍጽም የፈጠራ ድርሰት ስለሚሆን ፊንፊኔ በጭራሽ አዲስ አበባ እንዶጥና አይደለችም። የማስገበር ዘመቻው ከአንጎለላ ተነስቶ ጋራ ጎርፎን አልፎ ሰላሌ ሙገር የአባይ ገባር የሆኑትን ከረንዞ፣ ፊንጭያ፣ ጭያቲ እና ሩፊ ወንዞችን አቋርጦ ግብር እንከፍልም ብለው ያመጹትን የሰርቲ ጋላ (Serite Galla) ጎሳዎችን ለመስገበር ነበር።

በዚህም መሠረት የፊንፊኔና ኤካ ሸለቆዎች ከዛሬው እንጦጦ ተራራ በስተሰሜን ምዕራብ አቅጥጭያ ከመናገሻ ተራራ በስተምዕራብ ሰሜን እንጅ ዛሬ አዲስ አበባ በምትገኝበት ስፍራ አልነበሩም።

በአዲስ አበባ ከተማ የጉለሌ ሰፈርም ከሰላሌ ጉለሌ የመጡ ሰፋሪዎች ሰፈር ነው። ልክ ከጎላ፣ ከሞረት፣ ከጎጃም፣ ከወሎ፣ ከጋሞ ዶርዜ፣ ወዘተረፈ የመጡት ለሰፈራቸው ስም እንደሚሰጡት ማለት ነው።

የጉለሌ ነባር ነዋሪዎች ከአዲስ አበባ በምኒልክ ዘመን ተባረሩ አያልክ ትወሻክታለሁ።

አንድም የተባረረ ሰው የለም። የአዲስ አበባን ፍል ውሃ ያገኙት እቴጌ ጣይቱ ቡጡል እንጂ ሻምበል ሐሪስ ይሁን ሌላ ፈረንጅ ወይም አበሻ አካባቢውን የጎበኙት አልጻፉም፣ አልተናገሩም።

የሸዋ በተለይም የመናገሻ አውራጃ ማለትም እንደግብጣን የአዲስ አበባና እንጦጦ ዙሪያ ነባር ነዋሪዎች የኤካ፣ የፊንፊኔ፣ የጉለሌ፣ የአቢቹ ወዘተረፈ ቱላማ ጎሳዎች በጭራሽ አልነበሩም። እነዚህስ በሸዋ በ1567 ዓ.ም ቱላማዎች ከአዋሽ በስተሰሜን ያለውን አገር ወረው ያጤ ሚናስ አዝማች የነበረውን ዘርዕ ዩሐንስንና ጦሩን አውድመው ነባሩን ያማራ፣ የጉራጌ፣ የጋፋትና አርጎባ ሕዝብ ፈጅተውና አፈናቅለው በወረራ የሰፈሩ ነበሩ። ከግራኝ አሕመድ ጅሃዳዊ ወረራ መልስ የጋላ ቱላማና ሜጭያ ጎሣዎች በሉባ የደፈጣ ወራሪ ኃይል በየስምንት ዓመቱ ተመላልሶ በመዝረፍ፣ በመግደልና በመስለብ ነባሩን የእንደግብጣን (መናገሻ) አማራ፣ ጉራጌ፣ ጋፋት፣ አርጎባ፣ ከምባታ፣ ሃድያ ገበሬዎችን በገፍ ፈጅተው ለም መሬታቸውን ቀምተው በወራሪ ሰፋሪነት ተንሰራፍተዋል።

የቅርብ ዘመን መጤ ሰፋሪዎች እንጂ የሸዋና አካባቢዋ ቀዳሚ አቅኚ ነዋሪች በጭራሽ ባለመሆናቸው የኦሮሚያ ክልል ተብዬው በፍጹም ተቀባይነት የለውም። በወያኔና ሻዕቢያ ርድታና ትብብር በባንቱስታን አፐርታይድ የጎሣ ፖለቲካ ያለ ሕዝብ ፍላጎትና ስምምነት የተሳለው ፍጹም የፈጠራ ክልል "ኦሮሚያ" ከቶ ዘላቂነት አይኖረውም።

ዛሬ በሰፊው የሚነዛውና የሚቀነቀነው ፋሽስታዊና ዘረኛ ቅስቀሳ፡ "ኦሮሚያ ለኦሮሞ ብቻ፣ ፊንፊኔ የኦሮሚያ ዋና ከተማ ናት፤ የአዲስ አበባ መሪ እቅድ መስፋት ወይም ማደግ የለባትም፣ ነፍጠኞች ከዲስ አበባ ይውጡ፣ ያጤ ምኒኪክ ሐውልት ይፍረስ" እያሉ ከንቱ መቀናጣት ከፍተኛ መዘዝ ያስከትላል።

በርግጥም በወራሪነት፣ በተስፋፊ ቅኝ ግዥነት መጤ ሰፋሪዎች ራሳቸው ወረሞች ስለሆኑ አሳ ጎርጓሪ ዘንዶ አወጣ እንዳይሆን ቢያስቡበት ይበጃል።

ለምሳሌ ፖርቱጋልና እስፓኝ በአውሮፓ በአረብና በርበር እስላሞች ለብዙ ዘመናት ሲገዙ ቆይተው በ14ኘው ምዕተ ዓመት ነው አረብ እስላሞችን አባረው መልሰው መሬታቸውን ያቀኑት። በኢትዮጵያ የሸዋ ነጋሲዎች ከነጋሢ እስከ አጤ ምኒሊክ ያደረጉት ተመሳሳይ ነው። ከ16ኛው ምዕተ ዓመት በፊት የጥንት ኢትዮጵያ ግዛት አካል ያልሆነን ምድር አላስገበሩም።

ንጉሥ ሣህለ ሥላሴ ለሻምበል ሐሪስ እንደነገረው፣

በቅርቡ ወደ ጉራጌ ታላቁ ሕይቅ (የዟይ ሐይቅ) ዘመቻ አደርጋለሁ። በዟይ ሕይቁ ውስጥ ብዙ ደሴቶች ይገኛሉ። ያያት ቅድምያቶቼ ግምጃ ቤቶችን ይዘዋል። በወርቅ አምባር የተሞሉ እንስራዎች፣ ከዝሖን ጆሮ ቆዳ የተሠሩ አርባ ነጋሪቶች፣ ብዙ ታቦቶችና ሰባት መቶ የግእዝ መጻሕፍት በብል መበላት ለአደጋ የተጋለጡ መሆኑን ይገኛሉ....።

ምንም ተጻራሪ አይጠበቅም ነዋሪዎቹ አብዛኛው ክርስቲያን መነኮሳት ናቸው፣ ብዙ ጊዜም ጋብዘውኛል።

<< It is my intention shortly to undertake an expidition to the great lake in Gurage. In it be many islands which contain the treasures of my ancestors: There are jars filled with bracelets of solid gold. There are forty drums
made of elephants' ears, and many holy arks pertaining unto ancient churches, besides seven hundred choice Ethiopic volumes, ...

No resistance is to be anticipated, for the inhabitants, who are chiefly Christian monks, have ioften invited me. I must no longer delay to recover the lost wealth of my forefathers. ..>>

ሣህለ ሥላሴ እንግሊዞቼ ጀልባ እንዲሰሩላቸው እንደጠየቁት ሻምበል ሐሪስ ዘግቧል።

ጀርመናዊው ሉድቪህ ዩሐን ክራፍ በዚያው ዘመን ሸዋ የነበረው አንኮበር ላይ ከተገኛቸው ከምደረ ጉራጌ የመጡት ቄስ ላዕከ ማርያምን ጠይቆ እንደ መዘገበው በምድረ ጉራጌ ከሰላሳ ሰባት በላይ ገዳማት ይገኛሉ። በከምባታም ከአሥራ አምስት በላይ ገዳማት ሲኖሩ በወለሞም ብዙ ክርስቲያኖች እንዳሉ ነግረውታል። (J.L Krapf: Travels, Researches and Missionary Labour During an eighteen years Residence.. ( London, 1968) 2nd ed, PP. 97-100)

ንጉሥ ሣህለ ሥላሴም በደቡብና ምዕራብ ኢትዮጵያ የተበታተኑትን ሕዝበ ክርስቲያን እንድ ለማድረግ ዋና ተግባሩ እንደሆነ ለእንግሊዝ መልክተኞች ዘወትር መናገሩ ተጠቅሷል።

ንጉሡ ባመት ሦስት ጊዜ ዘመቻ እያደረጉ በግራኝ ጊዜ ተነጥሎ በደቡብና ምዕራብ ተብታትኖ የሚኖረውን ሕዝበ ክርስቲያን ሁሉ አንድ ለማድረግ፣ ያባቶቻቸውን ጥንታዊ ሃብትና ቅርስ ለማግኝት እንደሆነ ለሻምበል ሃሪስ ነግረውት በመጽሐፉ መዝግቦታል። (W.Harris: Highlands of Ethiopia (London, 1844, P. 134) )

የንጉሡ ሠራዊት ከአዋሽ ማዳ ሰዶን፣ የአይመለል ጉራጌ አካባቢን፣ ከረዩን፣ ጅሌንና ሌሎች ጎሣዎችን አስገብሯል። በጉራጌ ምድር ወደ ሚገኘው ትልቁ ሐይቅ (ዟይ) በቅርቡ ለመዝመት አስቤያለሁ በዚያም ያባቶቼ ወርቅና ዕንቁዎች ይገኛሉ። በዟይ ሐይቅ ደሴቶች ውስጥ 40 ነጋሪት ከዝሆን ጆሮ ቆዳ የተሠሩት፣ ጥንታዊ ታቦታት፣ ከሰባት መቶ በላይ የኢትዮጵያ የብርና መጻሕፍት በብል መበላት ጥቂቶቹ አደጋ ላይ መሆናቸውን ተነግሮት ጽፎታል። እንግሊዞቹ ጀልባ እንዲሰሩለት ጠይቋል።

በአጠቃላይ በሸዋም ከመንዝ ጀምሮ ደረጃ በደረጃ ሃይማኖትና ጎሣ ሳይለይ ይፋትን፣ ተጉለትን፣ ጠራን፣ ሞረትን፣ መራቤቴ ኮራን፣ ቡልጋን፣ ምንጃርን፣ ጉራጌን፣ ግራርያን፣ ዟይን፤ ከምባታን፣ ግንደበረትን፣ ወዘተረፈ መልሶ ለማቅናት ያላቋረጠ ዘመቻ ተደርጓል። የአርጎባ ወላስማ እስላምና የኦርቶዶክስ ክርስቲያን መሪዎች ተባብረው የሸዋን መንግሥት በጠንካራ መሠረት ገንብተውታል።

ታዲያ ይህች ችኮ መንቻካ ቦኒ ሆልኮምብ ፀረ ጥቁር "ኢትዮጵያ በኢምፔሪያሊስቶች ርድታና ድጋፍ የተፈጠረች አገር ናት" በማለት ከሁሉም በላይ የአድዋውን የጥቁር ሕዝብ ድል ዋጋ ለማሳጣት አዳክራለች። ይህች እጅግ በጣም ዝቃጭ ምሁር ተብዬ ጸረ ኢትዮጵያ ፕሮፓጋንዳዋን ስትቀጥል፤

<< .. the promotion of democracy by United States failed in Ethiopia due to the fundamental contradictions that exist between the Ethiopian colonizers and the colonozed peoples. (Bonnie k. Holcomb, The Tale of two Democracies 1997, Journals of Oromo Studie. Vol 4, 47-82)

ያሜሪካ እገዛ የዲሞክራሲ ግንባታ በኢትዮጵያ የከሸፈው በኢትዮጵያውያን ቅኝገዥዎችና ተገገዥዎች መካከል ባለው መሠረታዊ ቅራኔ ነው።>> በማለት ቀዠብራላች።

የሻምበል ሃሪስ መጽሐፍ (The Highlands of Ethiopia, 1844) የመጀመሪያው እትም ከተዘጋጀ በኋላ በልዩ ልዩ ቋንቋዎች ተተርጉሞ ይገኛል።

ታዲያ! ዶክተሬ ለምን ከምንጩ አንብበህ በትክክል አገናዝበህ ፍሬውን ከገለባው ለይተህ አላቀርብክም። በጠባብ የጎሣ ስሜት ዓይነ ሕሊናህ ስለምን ታወረ?

# የአፍሪቃ ምስል

ደግሞ ትልቁ ነገር እነሻምበል ሐሪስ እና ብጤዎች በነበሩበት ወቅት ያለውን አመለካከት /Zeitgeist/ አለማገንዘብህ ነው። የቀዳሚው 19ኛው ክፍለ ዘመን ያውሮፓውያን "የአፍሪቃ ምስል - image of Africans" ክጨዋ አረመኔነት " noble savage" ወደ ወራዳ አረመኔነት " ignoble savage" ተቀይሮ ጥቁር አፍሪቃ በጭካኝነት፣ በፈላጭ ቆራጭነት፣ በአጭበርባሪነት፣ በከዳተኛነት፣ በተጠራጣሪነት፣ በሥልጣኔየለሽነት፣ ባሕልየሽና ኋላቀርነት፣ በሰነፍና ሴሰኛነት ወዘተረፈ መገለጭያነት ዘረኞች የጥቁር ሕዝብ ጥላቻና ንቀት ነዝተዋል። የሻምበል ሐሪስ ሆነ የፕሮቴስታንት ወንጌል መልክተኛ ተብዬ ስላይ ሁሉ የጻፉት ትርኪ ምርኪ ያውሮፓ ዘረኞች ያፍሪቃ ምስላቸው እይታ ነው። ጥቁር አፍሪቃዊ ሆኖ የዘረኞችን ፀረ ጥቁር የውሸት ቁልል ሰምቶ ማራገብ ጠጣነት ነው።

ኢትዮጵያ በአፍሪቃ ጥንታዊ የጥቁር አገርና ነፃነቷ፣ ባሕሏና ሃይማኖቷን ጠብቃ ያውሮፓ ተስፋፊ ዘረኞችንና ዘመናዊ ወታደር በልጆቿ የጋራ መስዋዕትነት ድብቅ መታ በመምለሷ ምክንያት ዋና ጠላት ተደርጋለች።

# የማን ሕገ መንግሥት?

የወያኔ ኢሕአዴግና ተለጣፊ ጥርቅሞች ሕገ መንግሥትና የባንቱስታን የጎሣ ፌደራላዚም በኢትዮጵያ ምድር ልክ እንደ ወታደራዊው ድርግ ሶሻሊዝም ይቀበራል። ስለዚህ ዶክተር ነጋሶ በአንተ መሪነትና በሆዳም ባንዶ ተባባሪዎችህ የተቀነባበረው ሕገ መንግሥት ተብዬው ማወናበጃ ምንም ዋጋ ስለሌለው በሕገ መንግሡት መሠረት የኦሮሚያ በአዲስ አበባ ላይ የበላይነት ይከብር አያልክ የምትዘበዝበው ሁሉ ምንም ዋጋ የለውም። የባንቱስታን አፓርታይድ የጎሣ ፌደረላዚም ከወያኔ ጋራ ይወድማል። የኢትዮጵያ ሕዝብ በነፃ ምርጭያና በዲሞክራሲያዊ ሥርዓት የራሱን ሕግመንግሥት፣ ያስተዳደር ሥርዓት፣ ያካባቢና ማእከላዊ መንግሥት አወቃቀርን ይወሳናል።

በግልጽ እንደሚታውቀው ከመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ 45 ከመቶ የሚይዘውን ያማራውን ሕዝብ አግልላችሁ፤ ኤርትራን በማስገንጠል፣ የአፋርን ኢትዮጵያዊ ሕዝብ ከሁለት ሸንስናችሁ፣

ቀሪውን የኢትዩጵያ ምድር በጎሣ ቋንቋ መለያ ሽፋን ያለ ሕዝብ ነፃ ፈቃድና ስምምነት ልክ እንደ ፋሽስት ጣሊያን ከፋፍላችሁ፤ በኢትዩጵያ ታሪካዊ ጠላቶች ከፍተኛ ድጋፍና ትብብር የተመሠረተው የሽግግር ቻርተርና የሰፈነውን የአፓርታይድ የጎሣ ፖለቲካን ሆኖ ሳለ የወያኔ ኢሕአዴግ ተቃዋሚ ነን ብላችሁ ከብጤዎቻችህ ጋራ ስለ ሕጋዊነትና ሕገ መንግሥት ስትቦተልኩ በጣም ያስገርማል። በኢትዩጵያ የሰፈነውን የጎሣ ፌደራሊዝማና ያናሳ ጎሣ አምባገነን ሥርዓት ለማስወገድ በሁሉም ዓይነት የትግል ስልት ትግሉ ይካሄዳል። የኢትዩጵያ ሕዝብ በተባበረ ኃይሉ በወያኔ ኢሕአዴግ የጎሳ ፌደራሊዝም መቃብር ላይ ዲሞክራሲያዊ አስተደደር እንደሚገነባ ጥርጥር የለም።

በመሆኑም የአዲስ አበባ ሕዝብ በጠመንጃ አፈሙዝ የተነጠቀውን ራሱን በራሱ የማስተዳደር መብቱን ያስከብራል። ዲሞክራሲያዊ ሥርዓተ ማኅበር በኢትዩጵያ ተግባራዊ ይሆናል።

የአዲስ አበባ ከተማ የኢትዩጵያና የአፍሪቃ መድና ብቻም ስትሆን የሸዋ ክፍለ ሀገር ዋና ከተማ ናት። የመናገሻ አውራጃ ከሸዋ ክፍለ ሀገር ጠቅላላ ስፍት (85 ካሬ ኪሎሜትር) 11 ካሬ ኪሎሜትር ሲሆን አዲስ አበባም በዚሁ ውስጥ ሰለምትገኘ በሁሉም አቅጣጭያ መስፋትና ማደግ ትችላላች። ይህም የአዲስ አበባና በዙሪያዋ የሚኖረው የመናገሻ አውራጃ ሕዝብ ብቻ ነፃ ውሳኔ ነው። ያዲስ አበባን የመሳፍት ሂደት ማንም መግታት አይችልም።

ከሁሉ በተቀዳሚ የወያኔ የሊዝ ስርዓት አብሮት ይወገዳል። የግል ሃብት ይዞታ በሕግ ይረጋገጣል። ገበሬው የመንግሥት ጭሰኛ መሆን ያከትማል። በወያኔ ኢሕዴግ ካድሬዎች የመሬት ቅርምት የተዘረፈውና የሚዘረፈው፣ በወታደራዊ ደርግ ያላግባብ የተወረስ ሃብት ንብረት ለባለቤቱ ይመለሳል።

## ማጠቃላያ

"የኦሮሚያ ልዩ መብት በአዲስ አበባ ላይ" ተብሎ የሚለፈፈው በጭራሽ ተቀባይነት የለውም። መታወቅ ያለበት አዲስ አበባ የአዲስ አበባዎችና የሸዋ ተወላጆች ብቻ ናት። ስለሆነም ሌሎች በተለይም ወለጋዎች፣ ጅማዎች፣ አሩሲዎች፣ ቆቱዎች ወዘተረፈ በጭራሽ አያገባችሁም።

ሁሉም የወያኔ ወረሞ ኦሕዴድ ካድሬዎችና ተቃዋሚ ነንባይ እነ ቡልቻ ደመቅሳና ብጤዎቹ በሸዋ ምድር የሚያገባቸው ነገር አንዳችም የለም። አቶ ቡልቻ ያጤውና የደርጉ መንግሥት ታማኝ ግብረበላ ነበር። በዘመነ ወያኔ ኢሕአዴግ ደግሞ የፀረ አማራው ጥላቻ ቅስቀሳ አዝማች ፊታውራሪ በመሆን ዐማራውን በነፍጠኛነት፣ በቅኝ ገዥ ተስፋፊነት ፈርጃ ይንቦራቀቃል። ያማራውን፣ የጉራጌውንና ያርጎባውን ምድር ሁሉ እንደፈለጉትና አንደሚመኙት ያለምንም ተቃዋሞ አጠቃለው ሰፊ የኦሮሚያ የፈጠራ ክልል እንደሳሉት ሁሉ በትግሬ ክልል ተብዬው ውስጥ የሚኖሩት የራያና አዘቦ ጋሎች ልዩ ዞን ስለምን አልተከለለላቸውም ብሎ በወያኔ ትግሬ ላይ ከፍተኛ ቅሬታ ሲያሰማ ተደምጧል።

የወረሞ ጠባብ ጎሠኞች ሁሉንና ምርጡን ነገር ለወረሞ ብቻ ብለው ቅስቀሳ ያደርጋሉ። ነገር ግን ከፍተኛ የሕዝብ ቁጥር ብዛት ያላቸውን የናዝሬት፣ የአሰላ፣ የድሬዳዋ፣ የጅማ፣ የሐረር፣ የጎባ ወዘተረፈ ነዋሪ አማሮችና ጉራጌዎችን ዲሞክራሲያዊ መብት ረግጠዋል። በራሳቸው ቋንቋ እንዳይጠቀሙ፤ የግል ሃብትና ንብረት እንዳያዳብሩ፣ በአፓርታይድ የጎሣ ፖለቲካ የወረሞ ቅጥረኛ ካድሬዎች ታላቅ ደንቃራ ሆነውባቸዋል። ይህ ዓይነቱ መጠነ ሰፊ የመብት ጥሰት በደል በአስቸኳይ ካልቆመ በስተቀር ለሚደርሰው ርምጃ ተጠያቂዎቹ ወያኔዎችና ተለጣፊ ግብረበላዎች ናቸው።

በያለበት በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ያማራ ገበሬዎችን ባማራነታቸው ተለይተው ከመሬታቸው ላይ ሲፈናቅሉ፣ ሃብት ንብረታቸው ተዘርፈው ሲባርሩ በአዲስ አበባ ዙሪያ ያሉ "ኦረሞ ገበሬዎች" በአሥረኛው የአዲስ አበባ ከተማ መሪ እቅድ ሊፈናቀሉ ነው፣ ቋንቋቸው ሊለወጥ ነው ብለው

የዩኒቨርስቲ ተማሪዎች ጎራ ለይተው አድማ በመጥራት ከሁሉም በላይ ኦሮሞ ያልሆኑ ገለሰቦችን ማለትም ያማሮችን፣ የትግሬዎችን፣ የጉራጌዎችን የግል ሃብትና ንብረት ለይቶ መዝረፍ፣ ማውደም ከፍተኛ ወንጀል ነው። ለዚህ ዘረኛና ፋሽስታዊ ድርጊት ተጠያቂዎቹ የወረሞ ብሔረተኝነት አቀንቃኞችና ጥላቻ ነዥዎች ስለሆኑ ለፍርድ መቅረብ አለባቸው። ለጥፋው ሕይወት፣ ለወደመው ንብረት በሕግ ይጠየቃሉ።

## ስለዚህ መደረግ ያለበት፣

1. በባንቱስታን የጎሣ ፌደራሊዝም መቃብር ላይ ትክክለኛ ክፍለ ሀገራዊ መስተዳድር በሕዝብ ነፃ ውሳኔ መሠረት የአካባቢ አስተዳደሮች ማለትም የጎጃም፣ የሸዋ፣ የትግሬ፣ የወሎ፣ የሐረርጌ፣ የሰዳሞ፣ የከፋ፣ የወለጋ፣ የባሌ፣ የሰሜንና በጌምድር፣ ወዘተረፈ መመሥረት ነው

2. ዲሞክራሲያዊ ሥርዓተ መምግሥት ማቋቋም ሕዝብ የራሱን አስተዳደር ተረክቦ በሕግ አውጭ፣ በሕግ ተርጓሚ፣ በሕግ አስፈጻሚ አካሎች ተዋቅሮ የሁሉም ነገዶች ባሕልና ቋንቋ ተከብሮ የኢትዮጵያ ነፃነትና ልዕላዊነት ተከብሮ ይኖራል።

3. በኢኮኖሚው በኩል ይግል ይዞታ ተረጋግጦ፣ አላግባብ የተወረሱት ሃብት ንብረት የከተማ ቤቶች፣ የልማት ተቋማት፣ ላባለንብረቱ ይመለሳል። በዘመነ ወያኔ የውጭ ከበርቴዎችና የወያኔ ካድሬዎች የተቀረራመቱቱ ሰፊና ለም መሬት የከተማ ቦታ ይወረሳል።
4. የኢትዮጵያ ገበሬ የመሬቱ ባለቤት ሲሆን ብቻ የምግብ ዋስትና ይኖረዋል።
5. ትምህርት ለሁሉም እስከ 12ኛ ክፍል በፃ መዳረስ ይኖርበታል።
6. የአፋር ኢትዮጵያዊ ሕዝብ አንድነት በማንኛውም መንገድ ይረጋገጣል።

ኢትዮጵያ በልጆቿ መስዋዕትነት በነፃነቷ ለዘለዓለም ትኑር!!

ገለበው ሰንጎነ / ፕሮፌሰር
ዘብሔረ ጋሞ

# የሸዋ ክፍለ አገር

fig. 2 : Shoa and its *awrajja* before 1987

